የዘመን መለወጫ መንፈሳዊ አበባዮሽ መዝሙር

እሰይ ደስ ደስ ይበላችው ደስ ደስ ይበላችው
ቅዱስ _____መጣላችሁ ደስ ደስ ይበላችው
ደስ ብሎን መጣን ደስን ብሎን ጌቶች አሉ ብለን
ደስ ብሎን መጣን ደስ ብሎን እሜቴ አሉ ብለን
አበባዮሽ ቅድስት /ለምለም/ /2/
እንቆቅልሹን ንግስት ልትፈትን ሄዳ ንግስት
ንግሥተ አዜብ ንግስት እናት ማክዳ ንግስት
በልቧ ያለውን ንግስት አጫወተችው ንግስት
አስቀምጣ አበባ ንግስት እያሳተችው ንግስት
መዓዛው የሚሸት ከሁለቱ የቱ ነው አለችው ከሁለቱ
ንግሥት ሆይ ለጥያቄሽ ጥበብ አለሽ
ለሀገር አጋር የሚሆነውን ከልብ ሸተሸ
እንቆቅልሹን የሳባ ከበድም ቢለው የሳባ
ጥበብ ስላለው ንጉሡ ምስጢሩን ያቆየው ንጉሡ
ክፈት መስኮቱን ሰሎሞን ቢለው ለሎሌው ሰሎሞን
ገቡ ንቦቹ ሊቀስሙ ከአበባው አርፈው ከቤቱ
ለተጠየቀው በርግጥ ንጉሥ ሰሎሞን አንዳች
አልተሰወረም በእውነት
አደይ ቅድስት ሀገሬ እልል በይ
ኢትዮጵያ ዝናሽማ በዓለም ተሰማ /2/
ለፈጣሪዋ ንግሥት ምሥጋና አቅርባ ንግሥት
ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ንግሥተ ሳባ ንግሥት
ጥበቡን አይታ ንግሥት አደነቀችው ንግሥት
ወርቅ ሽቶውን ንግሥት ዕንቁ ሰጠችው ንግሥት
ንግሥት ሆይ ምስክር ሆንሽ ለሀገርሽ
የአምላክን የፈጣሪያችን ስሙን ጠርተሽ
የኢትዮጵያ ሰዎች ንግሥት ቁሙ በተራ ንግሥት
ስንዱ ሆነው ንግሥት ለዙፋን ክብሯ ንግሥት
በመስከረም ወር ንግሥት ሀገር ስትገባ ንግሥት
ይዘው ስጦታ ንግሥት የፈካ አበባ ንግሥት
አደይ የብርሃን ጮራ ለኢትዮጵያ አበራ
ኢትዮጵያ በታሪክሽ ጥንታዊት ነሽ /2/
ኢየሩሳሌም ንግሥት ደርሰሽ መጣሽ ንግሥት
እንኳን ለክብር ንግሥት ለዚህ አበቃሽ ንግሥት
ከአምላክ በረከት ንግሥት ፍሬ አግኝተሽ ንግሥት
ይዘሽ ስጦታን ንግሥት እንቁለጣጣሽ ንግሥት
ንግሥት ሆይ በታሪክሽ ክብር አለሽ
ልጆችሽ አበባዮሽ እያልን እናስታውስሽ /2/
የአባቶች ተስፋ የፃድቃን የነቢያት ትንቢት ለጽናት
የሙሴ ጽላት ለጸሎት የአሮን ክህነት ለፍትህት
የዳዊት መንግስት በጸጋ ይዘሽ የመጣሽ ከጥንት
አምስቱን ሀብታት ተሰጥቶሽ ለሀገር መሰረት በእውነት
አደይ ቅድስት ሀገሬ እልል በይ
ኢትዮጵያ በልጆችሽ ደስ ይበልሽ
በሕገ ልቦና ጥንቱን ፈጣሪን አውቀሽ ጥንቱን
ሕገ ነቢያትን ከዓለም ቀድመሽ ተቀበልሽ ከዓለም
በብሉይ ኪዳን ለጌታ መስዋዕት አቀረብሽ ለጌታ
ተስፋ ከአደረጉት ከአይሁድ ከእስራኤል ቀድመሽ
ከአይሁድ
ሕገ ወንጌልን በፊት ይዘሽ ተገኘሽ በፊት
ኢትዮጵያ ደስ ይበልሽ ትልቅ ጸጋ አለሽ
ሰለ ፈጸምሽ ሶስቱም ሕግጋት የፈጣሪሽን /2/
ከአለፈው ስህተት ሁላችን እንድንመለስ ሁላችን
አዲሱ አመት ለሁሉ መጣ _____ለሁሉ
ይህም ያልፍና በጊዜው ይመጣል ዮሐንስ በጊዜው
ሌላው ይተካል በጊዜው ዘመነ _____ በጌዜው
ወልደ ነጎድጓድ በጊዜው ሲደርስ ዮሐንስ ዮሐንስ
በዓመቱ መጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ
አደይ የብርሀን ጮራ በኢትዮጵያ አበራ
ኢትዮጵይ ባህል ቋንቋሽ የሚያኮራሽ /2/
ልጇ አበባ ልጇ አበባዬ አዬ ውዲቷ እናቴ
ልጇ አበባ እያለች እማማ አዬ ውዲቷ እናቴ
ምክሯን ሁሉ እኔ እንድሰማ አዬ ውዲቷ እናቴ
እያሻሸች እንድሆን ጤናማ አዬ ውዲቷ እናቴ /3/
አበባው ለምለም ቄጤማው ለምለም
ኢትዮጵያ እንዳንቺ የለም (ተዋህዶ) እንዳንቺ የለም
አብዬ ኸኸ ደሞ እማምዬ
መጣው ለሠላምታ ከቤት አሉ ብዬ
እንኳን ለዘመነ _____ አደረሶት ብዬ /2/
ይሸታል የዕጣኑ ጢስ ሲታጠን ከመቅደሱ
በመላዕክት ዜማ ካህናት ሲቀድስ ሲታጠን ከመቅድሱ
ከብረው ይቆዩ ከብረው ከዓመት አውደ አመት
ደርሰው
ቅን ታዛዥ ልጆች ወልደው በእምነት በምግባር
ጸንተው
ትሁት ሰው አክባሪ ሆነው የፍቅር ሸማ ለብሰው